Centre for Information Resilience

# ኢትዮጵያ ውስጥ ስለሚስተዋሉ በቴክኖሎጂ የተደገፉ ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች ላይ የተደረገ ጥናት ማጠቃለያ

መጋቢት 2016

ሴንተር ፎር ኢንፎርሜሽን ሬዚሊያንስ

Centre for Information Resilience (CIR)

# መግቢያ

በይነ- መረብ በተለይም የማህበራዊ ትሥሥር ድረ-ገጾች ግላዊ እና ማህበረሰባዊ ጉዳዮች ሰፊ እና ገንቢ ውይይቶች እንዲደረግባቸው እድል የመስጠቱን ያክል ስጋቶችንም ይዞ መጥቷል። ኢንተርኔት ለመረጃ ማሰራጫ፣ ለማህበራዊ መስተጋብር፣ ማህበረሰብ የማንቃት እንቅስቃሴዎች እና ለፖለቲካዊ ቅስቀሳዎች አማራጭ መንገድ ሆኖ የሚያገለግለውን ያህል፣ በቴክኖሎጂ የተደገፈ ሥርዓተ-ፆታ ላይ የተመሰረተ ጥቃትን (TFGBV) እና አድሎአዊ ድርጊቶችን በዘላቂነት የሚያስቀጥል መድረክ ሆኖ ሲያገለግል ይስተዋላል። የሴቶችን እና የልጃገረዶችን የኦንላየን ደህንነት በሚገባ ለማስጠበቅ እና በማህበራዊ ህይወት ውስጥ ትርጉም ያለው ተሳትፎ እንዲያረርጉ ለማበረታታት በቴክኖሎጂ የተደገፉ ሥርዓተ-ፆታ ላይ የተመሰረቱ ጥቃቶችን መዋጋት ያስፈልጋል።

በዚህም መሠረት የዚህ ፕሮጀክት ዋና ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

- በኢትዮጵያ የሚስተዋለውን በቴክኖሎጂ የተደገፈ ሥርዓተ-ፆታ ላይ የተመሰረተ ጥቃትን በማስረጃ  ማሳየት
- የመንግስት ተቋማት፣ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች፣ ማህበራዊ ሚዲያዎችን የሚያስተዳድሩ ኩባንያዎች እና ማህበረሰቡ ስለነዚህ ጥቃቶች የተሻለ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ማድረግ
- በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች እና የመንግስት ተቋማት ይህንን ችግር ለመፍታት ለሚያደርጓቸው እንቅስቃሴዎች እንደ ግብዓት የሚሆኑ ተግባራዊ ምክረ ሃሳቦችን ማቅረብ

ሴንተር ፎር ኢንፎርሜሽን ሬዚሊያንስ (CIR) ባደረገው ጥናት (research) እና በአዲስ አበባ ውስጥ ባደረጋቸው ተከታታይ ውይይቶች እና ወርክሾፖች፣ በኢትዮጵያ ያሉ ሴቶች እና ልጃገረዶች በቴክኖሎጂ የተደገፉ ሥርዓተ-ፆታ ላይ የተመሰረቱ ጥቃቶች እንደሚደርሱባቸው ለማረጋገጥ ችሏል። በውይይቶቹ ወቅት ተሳታፊ በነበሩ ተወያዮችም መካከል በኢትዮጵያ ያሉ ሴቶች ከፍተኛ በሚባል ደረጃ ጥቃቶች እና ትንኮሳዎች በድረ-ገፅ መድረኮች በኩል እንደሚደርስባቸው የጋራ እምነት ታይቷል። ከእነዚህም ጥቃቶች መካከል የጥላቻ ንግግሮች፣ የበቀል ፖርኖግራፊ እና ትንኮሳዎች ይገኙበታል። የጥናቱ ተሳታፊዎች ችግሩን ለመፍታት የሚረዱ መፍትሔዎች ላይ ለመድረስ በጉዳዩ ዙሪያ የመረጃ እጥረት መኖርን እንደ ቁልፍ ጉዳይ ጠቅሰዋል። ይህ ጥናትም ይህንን የመረጃ  ክፍተት ለመሙላት ያለመ ነው።

## በቴክኖሎጂ የተደገፈ ሥርዓተ-ፆታ ላይ የተመሰረተ ጥቃትን ማጥናት ለምን አስፈለገ?

እነዚህ በበይነ መረብ በኩል የሚቃጡ ጥቃቶች በብዛት በገሃዱ ዓለም ወይም መሬት ላይ የሚያየውን ጾታን መሠረት ያደረገ ጥቃትን ሲያባብሱ ይታያሉ።  ሴቶች ኦንላየን ላይ ደህንነት ካልተሰማቸው፣ መሬት ላይ በማህበረሰብ ውስጥ የሚኖራቸውን ተሳትፎ ሙሉ በሙሉ እና ትርጉም ባለው መልኩ እንዳያደርጉ ሊያግዳቸው ይችላል። ይህ መገለል የተለያዩ አሉታዊ ተጽእኖዎችን ሊያስከትል ይችላል፤ ለምሳሌም ሴቶች በወሳኝ ጉዳዮች እና ዲሞክራሲያ ግንባታ ሂደቶች ውስጥ አነስተኛ ውክልና እና ተሳትፎ እንዲኖራቸው ሊያደርግ ይችላል፡፡

ጥቃቶቹ የተሳሳቱ አመለካከቶች፣ ትርክቶች እና እምነቶች ውጤቶች ናቸው። ይዘታቸውም ማግለል፣ መድልኦ እና የሚያሳንሱ ቃላት እና ዓውድ ያካተቱ ሲሆን የተዛቡ ታሪካዊ፣ ሃይማኖታዊ፣ ፖለቲካዊ እና ባህላዊ አመለካከቶች ላይ ሊመሰረቱ ይችላሉ። የተዛቡ አመለካከቶች እና እምነቶች በብዛት ለሚስተዋሉ ቀጥተኛ ያልሆኑ፣ በግድ የለሽነት፣ ባለማስተዋል እና ባለማወቅ ለሚፈፀሙ ጥቃት እና ትንኮሳዎች መንገድ ይከፍታሉ፡፡ እነዚህ ሁነቶች ከፍ ሲል እንደ ድብደባ፣ እስራት፣ አልፎ ተርፎም ጾታዊ እና አካላዊ ጥቃቶች ከመድረሳቸው በፊት እንደ ስድብ፣ ትንኮሳ እና ዛቻን ለመሳሳሉ የቃላት ጥቃቶች መንገድ ይከፍታሉ። ጥቃቶቹ እነዚህን ወደመሰሉ ከፍ ወዳሉ ደረጃዎች ሲደርሱ ከባድ እና ዘላቂ የሆኑ አካላዊ እና ስነ-ልቦናዊ ጉዳቶችን በተጠቂዎቹ ላይ ጥለው ያልፋሉ። በተጨማሪም ሴቶች ከማህበረሰባዊ ተሳትፎዎች እንዲገለሉ በማድረግ፣ ውሳኔ ሰጪዎች በመረጃ ላይ የተመሰረተ ውሳኔ እንዳያሳልፉ እንቅፋት ይፈጥራል። በህዝብ አግልግሎት ዘርፎች ውስጥ የአመለካከት ብዝሃነት አለመኖር የአስተዳደር አካላትን ተቀባይነት ሊያሳጣ ይችላል። ስለዚህም ለዚህ ችግር የፖሊሲ መፍትሄዎችን ለመቅረጽ የነዚህን ጥቃቶች አይነት እና የሚዘወተሩበትን መድረክ ማጥናት እና መመርመር አስፈላጊ ነው።

## ጥናቱ ሁለት ክፍሎች አሉት፡-

## ሀ. የመጀመያው ጥናት “Silenced, Shamed and Threatened: the online abuse of women and girls who participate in Ethiopian public life” የሚል ርእስ ይዟል

ኢትዮጵያ ውስጥ ሴቶች እና ወንዶች የኦንላይን ጥቃት እና ትንኮሳ ሰለባ እንደሆኑ ምንም ጥርጥር የለውም። በዚህም ላይ ተመስርቶ CIR የኦንላይን ጥቃት እና ትንኮሳ ተፅእኖዎች ምን እንደሚመስሉ እና ጥቃት የደረሰባቸው ግለሰቦች ልምዶችን ለመመርመር ይህንን ጥናት አድርጓል። ለጥናቱም በጉዳዩ ላይ ከዚህ ቀደም የተደረጉ ጥናቶችን እንዲሁም የተለያዩ ሰነዶችን መርመሯል። በተጨማሪም በመገናኛ ብዙሃን፣ በሲቪል ማህበራት እና በሲቪል ሰርቪስ ውስጥ ቁልፍ ሚና ያላቸውን እና ለኦንላየን ጥቃቶች ተጋላጭ ከነበሩ 14 ሴቶች ጋር ቃለ-ምልልስ አድርጓል።

### ጥናቱ መነሻ ያደረጋቸው እና ለመመለስ ያለማቸው ጥያቄዎች

- **ይዘት እና መጠን፡** ምን ዓይነት ይዘት ያላቸው የኦንላየን ጥቃቶች በብዛት ይታያሉ? በጥቃት አድራሾቹ  የሚዘወተሩ ልዩ ትርክቶች አሉ ወይ? ጥቃትና ትንኮሳዎቹ በኢትዮጵያ ምን ያህል የተስፋፉ ናቸው? ድግግሞሹስ ምን ይመስላል?
- **መድረኮች፡** በየትኞቹ ማህበራዊ ትሥሥር ድረ-ገጾች/መደረኮች ላይ ነው ጥቃቶቹ/ትንኮሳዎቹ የሚሰነዘሩት? ጥቃቶቹ በአደባባይ መድረኮች (በትዊቶች፣ ይፋዊ የፌስቡክ ልጥፎች፣ ወዘተ)  ወይስ በቀጥታ የመልእክት አማራጮች (ዋትሳፕ፣ ሜሴንጀር፣ ቴሌግራም) ነው የሚሰነዘሩት?
- **አላማ/ግብ፡** ጥቃት ወይም ትንኮሳ አድራሾቹ ምን ለማሳካት ታሳቢ አድርገው ነው ጥቃቶቹን የሚሰነዝሩት? ከጥቃቶቹ ጀርባ ጥቃቶቹን የማስተባብሩ አካላት አሉ?
- **ተፅዕኖ፡** እነዚህ ጥቃቶች ኢላማ በተደረጉ ግለሰቦች ሙያ፣ የግል ህይወት እና ቤተሰቦች ላይ የሚያደርሱት ተጽእኖዎች ምን ይመስላሉ? በእለት-ተእለት ኑሯቸው እና በስራዎቻቸው ላይ የሚደርጓቸው እንቅስቃሴያቸው ላይ ጫና ፈጥረዋል ወይ?

የቃለ-መጠይቆቹ ተሳታፊዎች በምላሾቻቸው የጥቃቶቹ ይዘት፣ አላማ እና ተፅእኖ ጥቃቱ ኢላማ እንዳደረገው ግለሰብ ጾታ ይለያያል የሚል ምላሽ ሰጥተዋል። በብዛት ሴቶች እና ልጃገረዶች ላይ የሚደርሱ ጥቃቶች ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረጉ፣ በፆታ ሚናዎች ላይ ያተኮሩ፣ ማንነታቸውን ለማሳነስ ያለሙ እና ስነ-ምግባር የጎደላቸው ይዘቶችን ያዘሉ ትንኮሳዎች እንደሆኑ በምላሻቸው አጋርተዋል። በተቃራኒው በወንዶች ላይ የሚደርሰው ጥቃት በአብዛኛው በኢላማዎቹ ገለፃ፣ አመለካከት ወይም የፖለቲካ አቋም ላይ እንደሚያተኩር ተናግረዋል። ግኝቶቹም በኢትዮጵያ የኢንተርኔት ዓለም ጤናማ ያልሆነ መስተጋብር እንደሚስተዋል፤ በሴቶች ላይ የሚሰነዘሩ ጥቃቶች ይዘት ሴቶች እና ልጃገረዶች በህብረተሰቡ ውስጥ ባላቸው ሚና፣ በጎሳቸው፣ በፖለቲካ አመለካከታቸው፣ በግብረ ሰዶማዊነት በመፈረጅ እና በሃይማኖቶቻቸው ዙሪያ ላይ ያነጣጠሩ እና እንደሆነ ያሳያል።

ቃለ-መጠይቅ የተደረገላቸው ሴቶች እንዳስረዱት በኢንተርኔት ላይ በሚደርስባቸው ጥቃት/ትንኮሳ ሳቢያ በማህበራዊ ትሥሥር ድረ-ገጾች ላይ እንዲሁም ከኢንተርኔት ውጪ ያሉ ማህበራዊ እንቅስቃሴዎች ላይ ያላቸውን ተሳትፎ እንዲያቆሙ እና ዝምታን እንዲመርጡ መገደዳቸውን ገልጸዋል። የሴቶችን በየኦንላየን መድረኮች ላይ ትርጉም ያለው ተሳትፎ ለማጎልበት ደህንነቱ የተጠበቀ የኦንላየን ከባቢ መፍጠር አስፈላጊ እንደሆነ ጥናቱ አመላክቷል። ዘላቂ መፍትሔ እና ውጤትም ለማምጣት እንዲሁም  የኦንላይን ጥቃቶችን በሚገባ መልኩ ለመዋጋት ዋና ስልት መሆን ያለበት የችግሩን ስር ማድረቅ ለምሳሌ የተዛቡ የስርዓተ-ፆታ አመለካከቶችን በማቃናት፣ በፆታ ላይ የተመሰረተ መድልዎ በመከላከል እና የሴቶች ውክልና በሁሉም የህዝብ መድረኮች ላይ በማሳደግ እንደሆነ የጥናቱ ግኝት አሳይቷል።

## ለ. ሁለተኛው የጥናት ክፍል “Normalised and Invisible: An analysis of gendered hate speech on social media in Ethiopia” በሚል ርእስ የተሰነደ ሲሆን

ይህ ክፍል የመጀመሪያው ጥናት ላይ የተመሰረተ እና የመጀመሪያው ጥናት ግኝቶችን በሚያጠናክር መልኩ የተከናወነ ነው። ይሄኛው ክፍል በጥልቀት ያተኮረው በኢትዮጵያ በቴክኖሎጂ የሚደገፉ ፆታን መሰረት ያደረጉ የጥላቻ ንግገሮች ላይ ሲሆን፤ በሶስት የማህበራዊ ሚዲያ መድረኮች (ፌስቡክ፣ ቴሌግራም እና ኤክስ) ላይ የተጋሩ የማህበራዊ ሚዲያ ይዘቶችን መርምሯል። ከመጀመሪያው ጥናት ለየት ባለ መልኩ ይህኛው ክፍል ከፆታ በተጨማሪ በሌሎች ተደራራቢ ምክንያቶች ላይ በመመስረት ግለሰቦች ላይ የሚቃጡ የጥላቻ ንግግሮችን ላይ አተኩሯል። (ይህም ማለት አንዲት ሴት በፆታዋ ምክንያት ኢላማ ሆና እያለ በተጨማሪ ልዩ ጥበቃ የሚደረግላቸው ባህሪያት ማለትም አካል ጉዳተኝነት፣ ዘር እና ሀይማኖት ላይ ተመስርቶ በተደራቢ ምክንያቶች የጥላቻ ንግግር ኢላማ ስትሆን ማለት ነው።)

ለጥናቱ ናሙና የሚሆኑ ይዘቶችን ለመሰብሰብ ይረዳ ዘንድ 2,058 የሚሆኑ ጥላቻን ያዘሉ ቃላት በአራት ቋንቋዎች (አማርኛ፣ አፋን ኦሮሞ፣ ትግርኛ እና እንግሊዘኛ) ተለይተዋል። ቃላቶቹን ለመለየት CIR ተከታታይ ወርክሾፖች በአዲስ አበባ አካሂዷል። የተለዩት ቃላት ከጥናቱ ሪፖርት ጋር እንደ አባሪ ተያይዘዋል። በጥናት ትንተናው ወቅት በናሙናነት የተወሰዱት የማህበራዊ ሚዲያ ይዘቶች (ልጥፎችም) በሦስት ምድቦች ስር ተለይተዋል፤ ምድቦቹም የጥላቻ ንግግሩ ይዘት ዓላማ፣ የይዘቱ ዓይነት (ስድብ፣ ዛቻ፣ ጾታን ከተወሰኑ ባህሪያት ጋር በማስተሳሰር ወይም የጾታ እኩልነትን ያላገናዘቡ ) እና የይዘቱ አውድ (አፀያፊ፣ ጠብ አጫሪ፣ አሳናሽ (stereotypical) ወይም ፌዝ/መሳለቂያ) ናቸው፡፡

### ጥናቱ መነሻ ያደረጋቸው እና ለመመለስ ያለማቸው ጥያቄዎች

- **የይዘት ቅርፅ (አይነት እና ስሜት)**:- ምን ዓይነት ሥርዓተ-ፆታ ላይ ያነጣጠሩ የጥላቻ ንግግሮች በብዛት ይታያሉ? የነዚህ የጥላቻ ንግግሮች ከጀርባቸው ምን መልእክት ይዘዋል? የጥላቻ ንግግር ከፆታ ፆታ ይለያያል ወይ?

- **ተደራራቢ ጥቃቶች፡**- ፆታን እና ሌላ የተጠበቁ ባህሪያት ለምሳሌ አካል ጉዳተኝነት፣ ጎሳ እና የኃይማኖት ማንነትን መሰረት ያደረጉ የጥላቻ ንግግርች ከሌላ የጥላቻ ንግግሮች እንዴት እና በምን ይለያሉ?

- **ቦታ/መድረክ፡**- በፆታ ላይ የተመሰረተ የጥላቻ ንግግር ማህበራዊ ሚዲያ መድረክ ይለያያል?

ሁለቱም ጥናቶች ሴቶች ከወንዶች በተለየ መልኩ በቴክኖሎጂ የተደገፉ ጥቃቶች እና የጥላቻ ንግግሮች እንደሚደርስባቸው አረጋግጠዋል። በማህበራዊ ሚዲያ ላይ የተጋሩ ይዘቶች ላይ የተደረገው ትንተና እንደሚያመለከተው ሴቶች ከወንዶች የበለጠ የጥላቻ ንግግሮች ኢላማ ይደረጋሉ። የጥላቻ ንግግሮቹም በውስጣቸው የተሳሳቱ የስርዓተ-ፆታ አመለካከቶችን እና ፌዝ ወይም አሿፊ ቃላትን ያያዙ ናቸው። ወንዶችን ኢላማ የሚያደርጉ የጥላቻ ንግግሮች ለዘብ ያሉ እና የተለሳሱ እንደሆኑ ጥናቱ ያሳያል። ጥናቱ እንደሚያመላከተው ከስርዓተ-ፆታ በተጨማሪም ጥብቅ የሆኑ ባህሪያት በኦንላየን ላይ ለሚቃጡ ጥቃቶች ኢላማ እንደሚሆኑ ነው።

ጥናቱ ሴቶች ላይ ያነጣጠረ የጥላቻ ንግግር በሌሎች የማንነት ቡድኖች ላይ ከሚሰነዘር የጥላቻ ንግግር እንደሚለይም አረጋግጧል። ሴቶች ላይ የሚቃጡ የጥላቻ ንግግሮች የሴቶችን የበታችነት የሚጠቁሙ፣ የተዛቡ ጾታዊ አመለካከቶችን እና ትርክቶችን ያዘሉ እና ፌዝ የተቀላቀሉባቸው ሲሆኑ፤ በሃይማኖት እና በብሄር ሳቢያ ኢላማ ከሚደረጉ ግለሰቦች ላይ የሚቃጡ የጥላቻ ንግግሮች ጋር ሲነፃፀር ለዘብ ያሉ የከረረ ጥላቻን የሚያመላክቱ ይዘቶችን እንደሚይዙ ጥናቱ ያሳያል። በተጨማሪም ከኢንተርኔት ውጪ ያሉ ሁነቶች፣ ኢንተርኔት ላይ የሚደረገውን ውይይት እና የጥላቻ ንግግሮች ስርጭት ላይ ተጽዕኖ ያሳድራሉ የሚለውን አመለካከት የዚህ ጥናት ግኝቶች ይደግፋሉ። ለዚህም እንደማሳያ የሚሆነው ይህ ጥናት በተደረገበት ወቅት በአማራ እና በኦሮሚያ ውስጥ በነበሩት ግጭቶች ሳቢያ የሁለቱ ብሔር ተወላጅ ሴቶች ላይ ይቃጡ የነበሩት ተደራራቢ የጥላቻ ንግግሮች ከሌሎች ብሔረሰቦች ጋር ሲወዳደር በአንፃራዊነት ከፍተኛ ሁኔታ መስፋፋቱን ማየት ይቻላል። የፖለቲካዊ ክስተቶች ተከትሎ የሚሰራጭ ግጭት ቀስቃሽ ንግግሮችን የሚጠቀም የጥላቻ ንግግር ከሥርዓተ-ፆታ መሰረት ካደረገ የጥላቻ ንግግር የበለጠ ሊጎላ ይችላል።

አዲስ አበባ ላይ በተደረጉት ውይይቶች ወቅት መታየት የተቻለው አብዛኛውን ጊዜ በርካታ ሰዎች የጥላቻ ንግግሮችን በተሳሳተ መንገድ እንደሚረዱት እና በቴክኖሎጂ የተደገፉ ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች ችላ እንደሚባሉ ነው። በተጨማሪም አንዳንድ ይዘቶች ለምሳሌ የተዛቡ የስርዓተ-ፆታ አመለካከቶችን፣ ስድብ፣ አዋራጅ ቃላት፣ ወይም የሴቶች ከሌሎች ጾታዎች የበታች መሆናቸውን የሚያመላክቱ ንግግሮች፤ አደገኛ እና ጠብ አጫሪ ከሆኑ የጥላቻ ንግግሮች ያነሰ ጉዳት ያደርሳሉ የሚል እምነት እንዳለ ጥናቱ አመላክቷል። ስለዚህም የጥላቻ ንግግር ምን እንደሆነ እና ስለሚያስከትላቸው ችግሮች እና ጉዳቶች የተሻለ ትምህርት በኢትዮጵያ ውስጥ መስጠት አስፈላጊ እንደሆነ ጥናቱ አመላክቷል። የስርዓተ-ፆታ ጥቃት፣ የተዛባ አመለካከት እና መድሎ ያለበት አስተያየት፣ ከብዙሃን እይታ የተጋረደ ይመስላል። የጥናቱ ተሳታፊዎችም የስርዓተ-ፆታ ጥቃት በጣም የተስፋፋ በመሆኑ ትኩረት እስከሚነፈገው ድረስ የተለመደ ሆኗል የሚል እምነት አላቸው።

## ምክረ-ሃሳቦች

በዚህ ጥናት CIR በኢትዮጵያ ውስጥ ካሉ ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር የፖሊሲ እና በማህበረሰብ መሪነት ሊተገበሩ የሚችሉ ምክረ-ሃሳቦችን አቅርቧል። ጥናቱ እንደሚያመላክተው የጥላቻ ንግግር  እንደ አላማው እና ኢላማ እንደሚያደርገው አካል ይለያያል። እነዚህን ልዩነቶች መረዳት የሴቶችን የኦንላየን ደህንነት በተሻለ ሁኔታ ለማስጠበቅ ያለሙ የፖሊሲ መፍትሄዎችን ለመቅረጽ የመነሻ ሃሳብ ይሰጣል።

ግኝቶቹ ላይ በመመሰረት፣ የመንግስት ተቋማት በመረጃ ላይ የተመሰረቱ የፖሊሲ ውሳኔዎችን ለመስጠት፣ የማህበራዊ ሚዲያ የሚያስተዳድሩ ኩባንያዎች የይዘቶች ክትትል እና ግምገማ ጥረቶቻቸውን ለመፈተሽ፣ የሲቪል ማህበራት ለውትወታ ጥረቶቸው እንደ ግብዓት ለመውሰድ እና ማህበረሰቡም የትግበራ ጥሪ  ለማቅረብ  ሊጠቀሙባቸው እንደሚችሉ CIR ጠንካራ እምነት እና ተስፋ አለው።

## ግንቦት 1፣ 2016 በአዲስ አበባ ስለሚካሔደው ሁነት/ኮንፈረንስ

ኮንፈረንሱ የሴቶችን ኦንላየን እና ኦፍላይን ደህንነት በተሻለ ሁኔታ ለማስጠበቅ እየሰሩ ያሉ ግለሰቦች እና ድርጅቶችን በአንድ መድረክ ለማሰባሰብ ያለመ ነው። በመድረኩ በቴክኖሎጂ የተደገፉ ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶችን ለመከላከል የሚሰሩ፣ የጥላቻ ንግግርን መከላከል ላይ የሚሰሩ እንዲሁም በበይነ መረብ የሚቃጡ ጾታን መሰረት ያደረጉ ትንኮሳ ፈጻሚዎችን ተጠያቂ ለማድረግ እና የህግ ማእቀፎች እንዲዘጋጁ ውትወታ የሚያደርጉ ግለሰቦች እና ተቋማት ተሳታፊ ይሆናሉ።

ሁነቱ የጥናቱን ይፋ የማድረግ፣ የባለሙያዎች መፍትሔ ላይ ያተኮረ ውይይት፣ ኤግዚቢሽን እና በኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ተሟጋቾች ማእከል (Ethiopian Human Rights Defenders Center) የሚመራ የትግበራ ጥሪ ይደረጋል፡፡ ኤግዚቢሽኑ ስለሴቶች መብት፣ በኦንላየን የሚደርሱ ጾታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶችን እና የጥላቻ ንግግር ግንዛቤ ለማስጨበጥ እና ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ተቋማት እነዚህን ችግሮች ለመፍታት እያከናወኑ ያሏቸውን አበረታች ስራዎችን ለማሳየት ያለመ ነው። ሁነቱን በመጠቀም CIR እና አጋሮቹ ብሩህ ተስፋን ለማስፈን፣ አጋርነትን ለማሳየት እና በበይነ መረብ የሚቃጣ ጾታን መሰረት ያደረገ ጥቃት በትኩረት መታየት ያለበት እና መፍትሔ ማግኘት ያለበት ጉዳይ መሆኑን ለማመላከት ያለመ ነው።

Centre for Information Resilience